# የኢንጂነሩ ቀረርቶ!!

አስማማው ፈለቀ

07/30/14

የሰማያዊ ፓርቲ ልሣን የሆነው ነገረ ኢትዮጵያ ጋዜጣ በሐምሌ11 ቀን 2006 ዓ.ም እትሙ "የኢህአዴግ ማላገጫ መሆን አንፈልግም" በሚል የፓርቲው ሊቀ መንበር ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት የሰጡትን አስተያየት እንዲሁም ፓርቲው "መንግሥታዊ ሽብርተኝነትን የሚሸከም ትከሻ አይኖረንም" በሚል ርዕስ ሐምሌ 3 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን መግለጫ በማቀናጀት በዚሁ ፅሁፍ እንፈትሻለን፡፡

የሰማያዊ ፓርቲ መግለጫ መንግሥታዊ ሽብርተኝነት በማለት የገለፀው በውስጡ የተለያዩ አንኳር ጉዳዮችን የያዘ ነው፡፡ በህጋዊነት ተመዝግቦ የሚሰራውና የሚንቀሳቀሰው ይኸው ፓርቲ መንግሥትን በእኔ በኩል ሕጋዊ እውቅና አልሰጥህም ማለቱን በዘወርዋራ ገልፆታል፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ መንግሥታዊ ሽብርተኝነት የሚለው መንግሥት በሕዝብና በአገር ላይ ሊከሰት ያንዣበበውን የፀረ ሠላም ኃይሎችና የአሸባሪዎችን ድርጊት ለመከላከል በበቂ መረጃ እጃቸው አለበት ያላቸውን ሰዎች በህግ ቁጥጥር ሥር በማዋሉ ነው፡፡ ሽብርን መከላከል እንዴት መንግሥታዊ አሸባሪነት እንደሚሆን ሰማያዊ ፓርቲ ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ ሕገ ወጥ አዋጅ ሲል የኮነነው የፀረ ሽብር ህግና አዋጅ ቃል በቃል እነሱ ከሚያምኑባቸው ምዕራባውያን አገሮች በተለይም ከእንግሊዝ የተወሰደ በአሁኑ ወቅት ኃይማኖትም ሆነ ፖለቲካዊ አክራሪነት በቀጥታ ወደ አሸባሪነት እተለወጠ መሆኑን እነሱም አጥብቀው ያምኑበታል፡፡

ኢትዮጵያ እንደ አገር ከዓለም ሕዝብና ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተዋሀደ ሁኔታ የተቆራኘችና ብቻዋን ልትቆም የማትችል በመሆኗ ይህንን ዘመንና ወቅት የፈጠረውን የአሸባሪነት ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ አደጋ ለመከላከል ህጉን አውጥታ በሥራ ላይ አውላለች፡፡ እንደ ሌሎች አገራት ሁሉ ይህንን የአሸባሪነት አደጋ

የሚያጠናና ቅድመ መከላከል የሚያደርግ አገሪቱን ሕዝቧንም ከአደጋ የሚጠብቅ ልዩ ክትትል የሚያደርገው የፀጥታና ደህንነት ተቋምና የፖሊስ ኃይሉ ነው፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ ይህንን ሕጋዊ ተቋም ሕዝብንና አገርን ከጥፋት የሚከላከለውን የፀረ ሽብር ግብረ ኃይል ልክ ህገ ወጥ የማፊያ ቡድኖችና ወሮበሎች አድርጎ ማንነቱ የማይታወቅ የጨለማ ቡድን ወደ እሥር ቤት የሚያግዝ ሲል ገልጾታል፡፡

ሕጋዊ ሰውነት ያለው ሕጋዊ መታወቂያ ያላቸውን አካላት በዚህ መልኩ መፈረጅ የመንግሥትን ህልውናና ህጋዊነት አንቀበልም፤ አናውቅም ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለመንግሥት ህጋዊነት፣ ለህግና ለደንብ እውቅና አለመስጠት፤ ህግን መጣስ እንደ ትግል ስትራቴጂያቸው አድርገው እነ ግንቦት ሰባት የሚመሩበት የትግል መርህ ነው፡፡ የእነሱ ልሣን ፋክት መፅሔትና ሌሎችም ይህንንም ነጥብ አበክረው በተደጋጋሚ ገልፀዋል፡፡ ሰማያዊ ፓርቲ ቀድሞውንም የሚቀበለው በመሆኑ የተሸፈነበትን ሠላማዊ ካባ አውልቆ በይፋ ተቀላቅሎታል፡፡

ለሰማያዊ ፓርቲ ህጋዊ እውቅና የሰጠውን ለፀረ ሽብር ኃይሉም ሠላምና ፀጥታን የማስከበር ሀገሪቱንም ከውስጥና ከውጭ የአሸባሪዎች ሴራና ጥቃት እንዲከላከል ህጋዊ እውቅና የሰጠው መንግሥት ነው፡፤ሰማያዊ ፓርቲ ህጋዊ እውቅና የሰጠውን መንግሥት ህገ ወጥ ነው ካለ ሰማያዊ ፓርቲም ሕጋዊነት የለውም ወይንም በህግ ፊት እንደ አንድ ሠላማዊ ፓርቲ እውቅና የለውም ማለት ነው፡፡

ይልቁንም ግልጽ በሆነ መንገድ በህጋዊነትና በሠላማዊነት ሽፋን ተጠልሎ ከአክራሪና ፅንፈኛ ሙስሊም ኃይሎችን ጎን በመሰለፍ፤ የዓላማቸውና የትግላቸው አጋር በመሆን አልፎም አሁን ሰማያዊ ፓርቲ ይፋ ባወጣው መግለጫው መንግሥት በአሸባሪነት ለፈረጀው ግንቦት ሰባት ጥብቅና በመቆምና በመከራከሩ ማንነቱን ይበልጥ በአደባባይ ገልጿል፡፡ ሰማያዊ ፓርቲም አሸባሪ ፓርቲ ነው ማለት ነው፡፡

ለኢሣት የግንቦት ሰባት ሣተላይት ቲቪ ከባህር ማዶ ሥርጭቱ የሐሰት ፕሮፓጋንዳዎችን በመንዛት ፖለቲካዊም ሆነ ኃይማኖታዊ አሸባሪነት በአገሪቷ እንዲሰፍን፤ ሕዝብ ለአመጽና ለሁከት እንዲነሳሳ፤ በመንግሥት ላይ የኃይል እርምጃ እንዲወስድ፤ የእርስ በእርስ ግጭትና ሁከት እንዲነሳ፤ በፍጹም ጥላቻና ስሜታዊነት ተውጦ እልቂትና ደም መፋሰስ እንዲከሰት ለሊት ተቀን እየሰራ ላለው

ክፍል ሰማያዊ ፓርቲ ጥብቅና ቆሟል፡፡ እውቅና ሰጥቷል፡፡ ይህም ሰማያዊ ፓርቲ ከግንቦት ሰባት ጋር ያለውን ጥብቅ ቁርኝትና የዓላማና የተግባር ትስስር ያሳያል፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ ልሣኑ በሆነው ነገረ ኢትዮጵያ ጋዜጣ በተደጋጋሚ አመጽና ሁከት እንዲፈጠር፣ ወጣቱ በያለበት እንዲነሳ፣ ባለው አቅም ሁሉ በመንግሥት ላይ እንዲዘምት፣ የሞተው ሞቶ፣ ያለቀው አልቆ፣ የሚፈሰው ደም ፈስሶ አሁን ያለውን መንግሥት ከሥልጣን እንዲያወርደው ይህ ቀረሽ የማይባል ተደጋጋሚ ጥሪ ሲያደርግና ሲያሰራጭ ከርሟል፡፡

በዚህ ጭብጥ መሠረት ሰማያዊ ፓርቲ በሠላማዊ መንገድ የሚታገል ፓርቲ ሳይሆን አሸባሪ ፓርቲ ነው ማለት ነው፡፡ በአገሪቷ ውስጥ ሽብር እንዲፈጠር ያለማሰለስ እየሰራ ያለው ማነው? መንግሥት ወይንስ ሰማያዊ ፓርቲና ግንቦት ሰባት? ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ሙሉ በሙሉ በመደጋገፍ በየግሉ መጽሔቶች ሲሰሩ የቆዩት ሰማያዊ ፓርቲና መቀመጫውን አሜሪካ ያደረገው ግንቦት ሰባት መሆናቸው ግን ይታወቃል፡፡.

ሰማያዊ ፓርቲና ግንቦት ሰባት ቀን ቆርጠው ከመስከረም ጀምሮ የተቀጣጠለ ትግል በመላው አገሪቱ እንዲነሳ ወስነው እየሰሩና እያስተባበሩ ባሉበት በዚህ ወቅት መንግሥት ፖለቲካዊና ኃይማኖታዊ አሸባሪነትን የሚከላከል፣ የሕዝቡን ሠላምና ፀጥታ፣ ሐብትና ንብረት የመጠበቅና የማስጠበቅ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ አደጋው ከመከሰቱ በፊት የወሰደው እርምጃ መንግሥታዊ አሸባሪነት ሊያስብል አይችልም፡፡

ይልቁንም መንግሥትንም ሕዝብንም ለማሸበር በማቀድ ውስጥ ለውስጥ በመሥራትና በማሴር ቀን እየጠበቁ ረዥም ርቀት የተጓዙት ሕዝቡንም ለአመፅ በየመፅሄቶቻቸው፣ ፋክት፣ አዲስ ጉዳይ፣ እንቁ፣ ሎሚ፣ ጃኖ፣ ቆንጆ፣ አፍሮ ታይምስና ሌሎችም እንዲሁም በብሎገሮቻቸው፣ በየፌስ ቡኩ፣ በኢሣት ሣተላይት ቴሌቪዥን አማካይነት ዘረኛና ሠላም አደፍራሽ መልዕክት ሲነዙና ሲያስተላልፉ የቆዩት ሰማያዊ ፓርቲና ግንቦት ሰባት መሆናቸውን ተጨባጭ ማስረጃዎች አሉ፡፡

ይህ በአገሪቱ ጥፋት፣ እልቂትና ውድመት እንዲከሰት ለማድረግ ሰማያዊ ፓርቲ በሠላማዊነት ስም ሕጋዊ ፈቃድ ይዞ በአገር ውስጥ በፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም የጀርባ መሪነት፣ በኢንጂነር ይልቃል ጌትነት ፊት አውራሪነት፣

ግንቦት ሰባት ደግሞ አሜሪካ ተቀምጦ በዶክተር ብርሀኑ ነጋ ደጃዝማችነት በጋራ ያሴሩት የቃል ኪዳን ቁርኝት መረቡ መበጣጠስ ሲጀምር በሥደትና በፍርሀት የራደው ሰማያዊ ፓርቲ መንግሥታዊ አሸባሪነትን ለመመከት የሠላማዊ ትግሉን ደረጃ እናሳድጋለን ማለቱ ይበልጥ ማንነቱን ይፋ አውጥቶታል፡፡

በሌላ አገላለጽ በፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርም መሪነት የተመሠረተውና አሁንም ከጀርባ ሆነው በጦር መሪነት እቅድ በማውጣት የሚያዙት፣ በአዝማችነት በኢንጂነር ይልቃል ጌትነት የሚመራው ሰማያዊ ፓርቲ የግንቦት ሰባት ድርጅት የአገር ውስጥ ቅርንጫፍ ወይንም ተወካይ መሆኑን በይፋ አረጋግጧል፡፡ የአንዳርጋቸው ፅጌ ሰብዓዊ መብት እንዲጠበቅ በጥብቅ አሳስባለሁ ብሏል ሰማያዊ ፓርቲ፣ ዶክተር ብርሀኑ ነጋም በየትኛውም ቦታና ጊዜ እርምጃ እወስዳለሁ ሲል አቅራርቷል፡፡ ያልታደለች አገር መሰሪ የልጅ ጠላቶች ማለት እንዲህ ነው፡፡

የሰማያዊ ፓርቲ፣ የአንድነትና የአረና ትግራይ ፓርቲ አመራሮች በህግ ቁጥጥር ሥር መዋላቸውን የኮነነው ሰማያዊ ፓርቲ ሕወሐት/ኢህአዴግ የመጨረሻው መጨረሻ ደረጃ  ላይ መድረሱን ያረጋግጣል፣ አገዛዙ የሚከተለውን መንግሥታዊ ሽብር አቁሞ ለአገርም ሆነ ለራሱ የሚበጀውን መንገድ እንዲከተል አሳስቦ የታሰሩ የፖለቲካ ከፍተኛ አመራሮች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ጠይቋል፡፡ የግዴታ እኮ የዐረብ፣ የአልሸባብ፣ የአልቃይዳ፣ የቦኮሀራም፣ የአይሲስ አሸባሪ አንጠብቅም፣ የእኛም ሰዎች ወደዚሁ መንገድ ውስጥ ገብተዋልና፡፡

ገና ሦስት ዓመት ያስቆጠረችው ሰማያዊ ፓርቲ በእብሪት ተወጥራ ልትፈነዳ ደርሳለች፣ ከመሪው ጀምሮ እስከ አባላቱ ስለ ፖለቲካ ትግል እውቀትና ልምድ የሌላቸው፣ በስሜታዊነትና በጥላቻ ፈልተው የሚንተከተኩ፣ በአጉል ጀብደኝነት በጐረምሣ ልብና አስተሳሰብ ሜዳ አልበቃ ብሏቸው የሚያክላሉ ኮበሌዎች ናቸው፡፡ አለቃቸው ፕሮፌሰር መሥፍን በ90 ዓመት እድሜው ያልሰከነና ያልበረደ፣ እርጋታና ማስተዋል ለአዲሱ ትውልድ ማስተማር ያልቻለ፣ ጥፋትና እልቂት የተጠማ ሰው ነው፡፡ በዚህም ፖርቲውን እንደ ሌጣ ፈረስ እየጋለበ፣ በስሜታዊነትና በቅዠት እንዲዋትት እያደረገ ወደ አዘቅት እየነዳው ይገኛል፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ ቀስተ ደመና ፓርቲ ማለት ነው፡፡ ሳይጨመር ሳይቀነስ፣ በአጭሩ የሽማግሌና የጐረምሶች ስብሰብ የሆነው ሰማያዊ ፖርቲ ያልሰከኑ የፍንዳታዎች ፖርቲ ነው፡፡ በዚህም ነው እነ ኢንጂነር ይልቃል ገና በእድሜ ለጋ የሆኑትን ወጣቶች በማጥመድ ጥላቻ በጡጦ እየጋቱ በስሜታዊነትና በጀብደኝነት በበቀል እንዲነሱ በማድረግ፣ በአጉል ተስፋ እያጀገኗቸው ወጣት ነህ ተነስ፣ ታሪክ ሥራ፣ ታገል፣ ታሰር፣ ጀግና ነህ፣ እያሉ በፌስ ቡክ አርበኛነት በማበረታታት ጦማርያኑን ለተጠያቂነት አብቅተዋቸዋል፡፡ ሴራው የሰማያዊ ፖርቲና የግንቦት ሰባት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ትናንትም እንዲህ ነበሩ፣ በድሀው ልጅ ደምና ጉልበት ሲቀልዱ የኖሩት፣ ዛሬም እዚሁ ላይ ናቸው፡፡

ኢንጂነር ይልቀል መንግሥታዊ ሽብርን የሚመጥን ሠላማዊ ትግል ማድረግ እንዳለብን ወስነናል፣ የሥራ ማቆም አድማና የመሳሰሉትን በወቅቱ እንገልፀዋለን እለት በእለት ይላል፡፡ ኢንጂነር ይልቃል በጋዜጣው ላይ ባይገልፀውም በብዙ አጋጣሚ የተናገረው ነው፡፡ መጽሄቶቻቸው ደግሞ በብዙ እትሞች የቀለም አብዮቱ እንዴት መመራት እንዳለበት የሕዳሴው አብዮት፣ ኢሕአዴግ ይፍረስ በሚለው ፅሁፍ ፕሮፌሰር መሥፍንም ሌሎችም ደግመው ደጋግመው ለሕዝብ ለማሳወቅ ጥረዋል፡፡ መልዕክታቸውን አሰራጭተዋል፡፡

እናም ኢንጂነሩ ገለፀውም አልገለፀውም አስተሳሰባቸው ውጥንና እቅዳቸው ከቀበሌ ጀምሮ ወረዳ፣ ክፍለ ከተማ፣ አዲስ አበባና ክልሎች፣ በወጣቶችና በአዛውንቶች ያዋቀሩት - በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በሲቢክ ማህበራት፣ በነጋዴው፣ በተማሪው፣ በኃይማኖት ተቋማት፣ በግልና በመንግሥት ማምረቻ ድርጅት፣ በግሉ ሚዲያ፣ በሥራ አጡ ወጣት ውስጥ ገንዘብ በመደጐም የዘረጉት የሸረሪት ድርና ዓላማው በሚገባ እንደሚታወቅ ሁሉም ሊያውቁት ይገባል፡፡

ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የተመኛችሁት ሽብር፣ ነውጥ፣ ሥርዓተ አልበኝነት አንዲት ጋት ሳይራመድ ይመክናል፡፡ ሴራችሁ እንደ ቀትር ጤዛና ጉም ይተናል፣ ይበናል፣ ከእንግዲህ በአገርና በሕዝብ ሠላምና ደህንነት፣ ልማትና እድገት ላይ መቼም መቀለድና ማንቡዋለት እንደማይቻል ሕዝቡ የማያዳግም ትምህርት ይሰጣችኋል፡፡

የፖለቲካ አሸባሪነታችሁ የሕዝብን ሠላም ለማሳጣት፣ የተረጋጋ ሕይወት ከነቤተሰቡ እንዳይኖር፣ የግሉና የመንግሥት ኢኮኖሚ እንዲሽመደመድ፣ በመንግሥትና በግል አምራች ተቋማት የሚመረቱ ለሕዝቡ መሠረታዊ የሆኑ ሸቀጦች ምርት በአባሎቻችሁ አሻጥር እንዲስተጓጎሉ፣ ለሕዝብ እንዳይደርስ፣ በአባሎቻችሁ ትብብር የኢኮኖሚ አሻጥርና ደባ ውኃ፣ ቴሌ፣ የስልክ ችግር ሕዝቡ ውስጥ እንዲፈጠር፣ ለሕዝቡ እንዳይደርሱ የበለጠ ማጥፋት፣ በሱቆች የሸቀጥ እጥረት እንዲፈጠር በአባሎቻችሁ አማካይነት ነጋዴውን ይዞ እየተሰራ ያለውን ፀረ ሕዝብ ሥራ፣ የታክሲና የትራንስፖርት አገልግሎት (ሚኒ ባስ፣ ታክሲ፣ አውቶቡስ) አዲስ አበባና ክፍለ አገር እንዲቋረጥ አባሎቻችሁን በመጠቀም እየሰራችሁት ያለው አገር ገዳይ ሴራ በዝርዝር ይታወቃል፡፡

የትምህርት ሂደቱ እንዲቆም በቀንና ማታ ያሉትን ተማሪና መምህራን አባሎቻችሁን በመጠቀም እንዲስተጓጎል፣ ረብሻ ለመፍጠርና ትምህርት ለማቋረጥ፣ ገበሬው ምርቱን እንዳይሸጥ እንዲይዝ ወደ ከተማ እንዳያስገባ፣ ሕዝቡን ብስጭትና ውጥረት ውስጥ ለመክተት ገንፍሎ እንዲወጣ፣ የአገሪቱን ሠላም ለማናጋት የውጪ ኢንቨስተሮች የገቡት እንዲወጡ፣ ለመምጣት ያሰቡትም እንዳይመጡ እንዲሁም የአገሪቱን የቱሪስት ገበያ ለመግደልና የቱሪስቶች መዳረሻ እንዳትሆን፣ ዲፕሎማቶች ሥጋት ላይ እንዲወድቁ፣ ፍንዳታዎች ማድረስ፣ የመንግሥት ኃላፊዎችና ታዋቂ ሰዎችን ዒላማ ማድረግ አደጋ ማድረስ ወዘተ አቅዳችሁ እየሰራችሁ ነው፡፡ ሳትጀምሩት ተቀድማችኋል፡፡ እጁን አጣጥፎ የአገሩን ሞት የሚያይ መንግሥትና ሕዝብ የለም፡፡

የገዢው ፓርቲ አባላትንና ደጋፊዎችን ከማህበራዊ ሕይወት መነጠል፣ በመንግሥት ተቋማትና የንግድ ማዕከሎች የገዢው ፓርቲ ደጋፊ ናቸው ከተባሉ የንግድ ድርጅቶች የግለሰብ ንግዶች አለመግዛት፣ አለመጠቀም፣ ለሊትና ቀን በየቦታው የአመፅና የተነሱ ጥሪ ያዘሉ ወረቀቶችን መበተን፣ በተዋቀሩ የእሪታ ኮሚቴዎቻችሁ አማካይነት በየምሽቱ አዲስ አበባን ከቻላችሁ የክልሎች ከተሞችን በጩኸትና በእሪታ ማናወጥ፣ ፖሊስ ጣቢያን በመውረርና መሣሪያ በመዝረፍ፣ ባንክ የንግድ ተቋማትን፣ ታዋቂ ግለሰቦችን መዝረፍ ወዘተ የሰማያዊ ፓርቲና የግንቦት ሰባት ድርጅት አባላቶቻቸውን በመጠቀም ሊፈፅሙት የተሰናዱት ታላቅ በአገርና በሕዝብ

ላይ ያነጣጠረ የአሸባሪነት አደጋና ወንጀል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ተቀድሞችኋል፡፡ ከዚህ የከፋ አሸባሪነትና አክራሪነት ሌላ ምን አለ?

ይህንን የለየለት የሕዝብንና የአገርን ሠላምና ፀጥታ እንዲሁም ሉዓላዊነት የሚያናጋ በተቃዋሚነት ስም ሊካሄድ ዝግጅቱ የተጠናቀቀ ታላቅ የአሸባሪነት ወንጀል ለመከላከል እርምጃ መውሰድ በየትኛውም መሥፈርት መንግሥታዊ ታላቅነት እንጂ አሸባሪነት ሊሆን አይችልም፡፡ አሸባሪዎቹ ይህን ታላቅ ደባ በሕዝብ ላይ ለመፈፀም የግሉን ሚዲያ በመጠቀም ረዥም ጊዜ ሠላማዊ መስሎ ውስጥ ውስጡን ሲሰራ የቆየው ሰማያዊ ፓርቲ በሠላማዊ ስም ሕጋዊ ፈቃድ ይዞ የቀበሮ ባሕታዊ ካባ አጥልቆ ሲንደፋደፍና በመዲናችን ሲያቅራራ ግንቦት ሰባት አሸባሪ ድርጅት ደግሞ በሰማያዊ ፖርቲ ካባና ሽፋን ሥር በመሽጐጥ ተጠልሎ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገፅታዎች በመሆን ለረዥም ጊዜ ሲያሴሩና ሲዶልቱ ቆይተዋል፡፡ ሠላም ወዳድና አፍቃሪ ለሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለደግነቱ ለፍቅሩና ለርህራሄው፣ ለኩሩና ለጀግንነቱ ተቆርቋሪ ልጆችህ ነን የሚሉ አውሬዎች ጥልቅ ጉድጓድ ቆፍረው በውጪ ኃይሎች ተላላኪነትና ጉዳይ አስፈፃሚነት ተሰልፍው ከነቤተሰቡ ሊቀጥፉት ሲነሱ እነሱን የሚሸከምበት አንቀልባ፣ እሹሩሩ የሚልበት የአባት ወይንም የእናት ክንድ የለውም፡፡

አገሪቱንም፣ ሕዝቡንም ታላቅ ቀውስና ጥፋት፣ የማይወጣበት ቁልቁለትና አዘቅት ውስጥ ሊከቱትና ሊደፍቁት፣ ዳቦና ሠላም ናፋቂ፣ ተረጂና ተመፅዋች ስደተኛ ሊያደርጉት፣ ከሠላማዊ ኑሮው ቤትና ንብረቱ ሊያፈናቅሉት የወላድ መሀንም ሊያደርጉት እነ ሰማያዊ ፖርቲና ግንቦት ሰባት እልቂት ደግሰው በእብሪት ተወጥረው ያናፋሉ፡፡

ይህንን የማይቀበለው የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ እነዚህን ከአክራሪ እስላማዊ ኃይሎች ጋር ተቃቅፈው አገሪቱን የአሸባሪዎች ማዕከል ለማድረግ እየተክለፈለፉ ያሉ ቅጥረኞች ያለአንዳች ምህረትና ርህራሄ ድባቅ ይመታቸዋል፡፡ በነጉድጓዳዊና መብረቃዊ ኃይሉም ያጎናቸዋል፡፡ ሥውርና ገሀድ ጦርነት ካወጀ የአሸባሪ ኃይልና ቡድን ጋር አንድም ምንም ድርድም የለም፡፡ መንግሥትና ሕዝብ ሠላምን እንደሚያከብሩና እንደሚወዱ፣ ለሠላምም ተገዥ የመሆናቸውን ያህል ሠላምን ለረገጡ፣ ሠላምን ለማደፍረስ እየተሯሯጡ ላሉ ኃይሎች የሚሰጠው ምላሽ በእጅጉ

የበረታ ይሆናል፡፡ ከሚጠብቁትም በላይ ይሄዳል፡፡ ወደሠላማዊ መንገድና አስተሳሰብ ለመምጣት ውሣኔው የእነሱ ቢሆንም 11ኛው ሰዓት እያለፈ መሆኑን መረዳት ይገባቸዋል፡፡ የተሰመረውን ነጭ ሠላማዊ መስመር ሙሉ በሙሉ አልፈው ቀዩ መስመር ውስጥ ገብተዋል፡፡

ይህም ፈንጂና ተኩስ ወረዳ ውስጥ መግባታቸውን ያረጋግጣል፡፡ በዚህ ጣታቸውን ማንም ላይ ሊቀስሩ አይችሉም፡፡ ኢንጂነር ይልቃል ኢሕአዴግ ቆራጥ ነው፤ እኛም ቆራጥ ነን...ደም ዋጋ ጨምሮ ለመክፈል ግድ ይለናል፡፡ የልጆች ጨዋታ በሆነ ምርጫ ውስጥ አንገባም... ወዘተ ብለዋል፡፡ የኢንጂነሩ ጥሬ አባባሎች ያልተገሩ ናቸው፡፡ የቆፈራችሁት ጥልቅ ጉድጓድ ርቀቱን ልኩን ለራሳችሁ በሚበቃ መልኩ ገምቱት፡፡